<u>በፖለቲካ አስተሳሰብ ብዝሀነት ውስጥ የፖለቲካ ፓርቲዎች ዳርቻ</u>

ብእር ከአቃቂ ቃሊቲ

በምርጫ 2002 ሂደት ክርክሩን በሚገባ እየተከታታለ የገኘው ፓርቲና የተቃዋሚዎች ቁልፍ መልእክቶች እጨመቀ ያስቀምጥ የነበረ አንድ ጓደኛየ የተለየ አተያይ ነበረው። በመጨረሻም ተቃዋሚዎች ከኢህአዴግ ጋር ያደረጉት  ክርክር በዋነኛነት ህገ መንግስቱ ይሻሻል አይሻሻል በሚል ሪፈረንደም ይካሄድ የማለት ያህል ነበር በማለት ዋነኛ ጭብጥ ያለውን ለማውጣት ሞከረ። ይህንና የከሰሞኑ የተቃዋሚዎች ወገን የሆኑ ፀሃፊዎች ተቃዋሚዎች ነበሩባቸው በማለት ማነሳሳት በጀመሩት የድክመት ርእሰ ጉዳይ ጋር በማገናዘብ በኔ በኩል የተሰማኝን ላቅርብ ።

ከሰሞኑ ተቃዋሚዎች ለምን በምርጫ 2002 ለምን ተሸነፉ የሚል ጥያቄ በማንሳት በድረ ገፅ የሚቀርቡት ፁሁፎች አንድ አስገራሚ የሚመስል ለውጥ ማሳየት ጀምረዋል። በአንዳንድ የኢትዮጰያ ብሎጎች በስፋት ፀሁፋቸው ከሚያሰራጩና የተቃዋሚዎች መሸነፍ የተሳሳቱ ውጫዊ ምክንያቶች ሲሰጡ ከቆዩት ሳይቀር ተቃዋሚዎች ውስጣቸውን ይመልከቱ የሚል ጉትጎታ ጀምረዋል።

<u>የጉትጎታው አውንታዊ ገፅታዎች</u>

የድረ ገፅ ፀሃፊዎች ጉትጎታ የሚጀምረው ለተቃዋሚዎች ሽንፈት ይሆናሉ የሚሉትን ምክንያት በማቅረብ ነው። ከምክንያቶቹ መካከል ተቃዋሚዎች ራሳቸውን እንዲያዩበት የሚወተውት ነው። የተከፋፈሉበት ሚስጥር ፈትተው አንድ እንዲሆኑ የሚማፀነው ርእሰ ጉዳይ። ይህ ርእሰ ጉዳይ በምርጫው ሂደት ሲወድቅ ሲነሳ የነበረ ቢሆንም አሁንም እንደ ርእሰ ጉዳይ እንዲዘልቅና ተቃዋሚዎች የሚጠናከሩበት ምክር የመለገስ ያህል ተደርጎ የሚወሰድ የተቆርቋሪነት ስሜት ሆኖ ሊወሰድ ይችላል። አንድ ዜጋ ለሚደግፈው አካል እንዲህ አይነት ተቆርቋሪነት ለምን አሳየህ ተብሎ የሚነቀፍበት አንዳችም ምክንያት ባለመኖሩ እንደ አወንታዊ ገፅታ መወሰድም ተገቢ ሊሆን ይችላል።

በሁለተኛ ደረጃ ተቃዋሚዎች ራሳቸውን እንዲያዩ በነዚህ ወገኖች የቀረበው ምክር ደግሞ የመመረጥ ቴክኒካዊ ብቃታቸው ይፈትሹ የሚል ሆኖ እናገኘዋለን። እንደ ኢህአዴግ በሚገባ የተቀመረ የምርጫ ስትራቴጂ አልነበራቹህም የሚል እንድምታ አለው ይህኛው

ተቆርቋሪነት።ይሀኛው ንኡስ ርእሰ ጉዳይ ለማጠቃለል ያህል ተቃዋሚዎች ውስጣቸው ይመልከቱ የሚለው ተቆርቋሪነት አንድ አውንታዊ ገፅታ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። እንድምታው ተቃዋሚዎች ከሚደግፉ ወገኖች በኩል አንዳንድ ተቃዋሚዎች ለድክመታቸው ብዙን ጊዜ ኢህአዴግን አንዳንዴም ህዝቡ ምክንያታዊ ሆኖ አልመረጠም በሚል የሚያቀርቡት ምክንያት ላይ መሰላቸትን መፍጠሩ ነው። እናም ውስጣቹህን ተመልከቱ የሚለው የተቃዋሚ ፓርቲዎች ደጋፊ የድረ ገፅ ፀሃፊዎች በአወንታ የሚወሰድ ገፅታ አለው የምለው ለዚሁ ነው።

<u>አውንታዊ ገፅታዎቹ ከግንጥል ጌጥነት ለመታደግ</u>

እነዚህ ጉዳዮች በግልፅ መንገር የሚያስፈልገው በዚህ አገር የፖለቲካ አስተሳሰብ ብዙኃንነት /pluralism/ ተቀብሎ እነዚህ የተለያዩ ጥቅሞች ላይ መሰረት አድርገውና ተደራጅተው የሚንቀሳቀሱ ፖለቲካ ሃይሎች የእስከ አሁኑ ሂደታቸው በግልፅ ማሳየት ተገቢ ስለሆነ ነው።

የፖለቲካ አስተሳሰብ ብዙኃንነት በዴሞክራሲያዊ ፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ የተለያዩ አመለካከቶች ወይም አስተሳሰቦች ዕውቅና አግኝተው የሚንሸራሸሩበት ሁኔታን መፍጠር መሰረት ያደረገ ሂደት ውስጥ ከገባን 19ኝ አመታት አስቆጠርን። ይህ ሂደት ህገ መንግስታዊ እውቅና አግኝቶ ደረጃ ከፍ ካለበት ዘመን ጀምሮ እንቁጠር ካልንም 16 አመታት ብለን ልናሰላው እንችላለን።

ብዙኃነት በፖለቲካ ርዕዮተ ዓለምነቱ የፖለቲካ ሥልጣን በኅብረተሰቡ ውስጥ ባሉት መራጮች ብቻ ሳይሆን በሌሎች አካላት ጭምር ተሰራጭቶ እንደሚኖር ይገልጻል።ብዙኃንነት የሃሳብ ፍጭት ለማካሄድ የሚያስችል ድርድርን ያስቀድማል።ብዙኃንነት ድርድርና ከድርድር ሂደት በኋላ ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍሎች ሊያግባባ የሚችል የጋራ መግባባት ላይ ለመድረስ እንደሚቻል ተስፋ አድርጎ ይንቀሳቀሳል። ለድርድርና ለመግባባት ሰፊ ዕድል በመስጠትም ያምናል። እዚህ ላይ የ2002 ምርጫ ሂደት መግቢያ ላይ በሰጥቶ መቀበል ላይ የተመሰረተው የስነ ምግባር ደንብ መፅደቅና ይህንን ተከትሎ የተመሰረተው የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ልብ ይሏል።

አንድ ቡድን የያዘው አቋም በሁሉም አካላት ዘንድ ተቀባይነት ያለው አድርጎ ሊወስድ ውይም ሊቆጥር ይችላል። ነገር ግን በብዙኃንነት በሃሳብ ፍጭት ሂደት የሚገኘው ውጤት የአንዱ

ቡድን ወይም ተቀራራቢነት ያላቸው ቡድኖች የሚወክለው አስተሳሰብ ገዢ ሆኖ ይወጣል። ይህ ማለት ገዢ ሀሳብ ህግ ይሆናል ህጋዊ እውቅናም ያገኛል ማለት ነው። ሆኖም የአንዱ ቡድን ወይም ተቀራራቢነት ያላቸው ቡድኖች አስተሳሰብ ተከታዮች ያልተገባ ነገር ሳያደርጉና አንድን ቡድን ሳያጥላሉ አብሮ መሥራትን መቀጠል እንዲሁም ለቀጣይ የሃሳብ ፍጭት መዘጋጀት ግድ ይላቸዋል ማለት ነው። ይህ ነው እንግዲህ የአስተሳሰብ ብዝሃነት የሚተነትኑ የዘርፉ ባለሙያዎች ትርጉምና ከዚህ ትርጉም የሚቀዳ የመድብለ ፓርቲ ስርአት ቁልፍ አምድ መተንተኛ ነጥብ።

በሃሳብ ፍጭት አልፎ ያሸነፈ ሃሳብ ህጋዊ እውቅና ማንም ሊነፍገው የሚችል አለመሆኑ እርግጥ ቢሆንም ከባድ ሃላፊነት የመሸከም ብቃት ደግሞ ማሳየት ይጠበቅበታል። የአንዱ ቡድን ወይም ተቀራራቢነት ያላቸው ቡድኖች አስተሳሰብ ተከታዮች ያልተገባ ነገር ሳያደርጉና አንድን ቡድን ሳያጥላሉ አብሮ መሥራትን መቀጠል እንዲሁም ለቀጣይ የሃሳብ ፍጭት መዘጋጀት የሚለው የብዙህነት ሁለተኛው ዘውግ ይህንን ያሰምርበታል።

ለዚህ የአስተሳሰብ ብዝሃነት ዘውግ ከኢህአዴግ ወገን የተሰጡ ምላሾች በምርጫ 2002 ማግስት እንመልከት። ኢህአዴግ ቀድሞም ቢሆን የተነሳለትን የመድብለ ሥርዓት ፖለቲካ ሥርዓትን የመዘርጋትና የማዳበር ተልዕኮውን ለአፍታም መዘንጋት እንደማይፈልግ በምርጫው ማግስት አረጋግጧል።የመረጠውንም ሆነ ያልመረጠውን ሕዝብ በእኩልነት ለማገልገል ቁርጠ መነሳቱን የሕዝቡን አደራ ተቀብሎ ተቀብሎ በበለጠ ትጋት ለመሥራት እንደሚፈልግ የኢህአዴግ ሊቀመንበር ገልጸዋል

ተቃዋሚዎች በምክር ቤቶች ያላቸው ወንበር ብዛት በአገሪቱ የተዘረጋውን የመድብለ ፓርቲ ሥርዓት ለማሞቅም ወይም ለማቀዝቀዝ የመጨረሻ አማራጭ እንዳልሆነም ድርጅቱ አስታውቋል።ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ዛሬም ነገም በአገር ጉዳይ ከገዢው ፓርቲ ጋር ሊነጋገሩባቸው የሚችሉ በርካታ ጉዳዮች አሉ ተመካክረው ሊሰሩባቸው የሚችሉ ነገሮችም አይጠፉምና።

ከነዚህም መካከል የተጀመረውን የጋራ ምክር ቤት አሰራር መቀጠል አንዱ ሊሆን ይችላል በዚህ አሰራር የጋራ ጉዳዮችን በመተለምና በመንደፍ ተፈጻሚ የሚደረጉበትን ሁኔታ መፍጠር ይቻላል።በተግባር የሚገለጽ መከባበርና መቻቻል ያለበት የፖለቲካ ሥርዓት በመዘርጋትና

ተቃዋሚዎችም በአገሬ ጉዳይ ያገባኛል በሚል መንፈስ ንቁ ተሳትፎ በማድረግ መሥራት ይችላሉ ቀናነትና መግባባቱ ካለ በምክር ቤት ወንበሮች ብዛት ሳይሆን ውጭም ሆኖ ብዙ መሥራት ይቻላል።

**የተቃዋሚዎች መሸነፍ ሚስጥሮችና የብዝሃ አስተሳሰብ አንድምታ**

በአንድ ሀገር ብዝሃ አስተሳሰብ አለ ማለት የጋራ መግባባት የተጀመረባቸውና እየተጠናከሩ የሚሄዱ የጋራ እሴቶች የሉም ማለት አይደለም። ለምን ተቃዋሚዎች በ2002 ምርጫ ከክልልና ከፌደራል ፓርላማ ጥርግርግ ብለው ሊባል በሚችል ሁኔታ ወጡ ለሚለው ጥያቄ ሚስጥር የሚፈታውም ይህንኑ የብዝሃ አስተሳሰብ የጋራ እሴት ከኢትዮጲያ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አፍታትቶ በመመለስ ነው።

የኢትዮጲያ ህዝቦች እንደ ማንኛው በዴሞክራሲ ስርአት የሚመራ ሀገር ብዝሃ አስተሳሰብ የሚያስተናግዱበት የራሳቸው መዋእል ያላቸው የመሆኑን ያህል መግባባት የጀመሩበትና እያጠናከሩበት ያሉ አንድ ጉዳይ አለ። ህገ መንግስት። ይሀው ህገ መንግስት የሁሉም ህዝቦች እሴት መሆኑና ይበልጥኑ መግባባት እየደረሰበት ያለ ቢሆንም ከዚሁ በመለስ ባሉ ጥቅሞችና አስተሳሰቦች ብዝሃነት የለም ብሎ የሚዘጋ አለመሆኑንም ልብ ይሏል። የሀገራችን ተቃዋሚዎች የ2002 ምርጫ ሂደት ያለፉት የተለያዩ ጥቅሞች የሚወክሉ የብዝሃ አስተሳሰብን ፈለግ በመከተል ነበርን? ነው አደለም ለማለት በቅድሚያ ያነስዋቸው የነበሩ ሶስት መሰረታዊ ጎዳዮች እንመልከት። እነሱም የብሄር ብሄረሰብቦች መብት፣ የቡድን መብት፣ የመሬትና የሰላም ጥያቄ ናቸው።

1. **አንቀፅ** 39

ይህ የህግ መንግስቱ መሰረት የሆነው አንቀፅ በአሁኑ ወቅት ሁሉንም የኢትዮጲያ ህዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው እንዲያስተዳደሩና የአከባቢያቸው ጉዳይ በቅርበት ባደራጁትና ከክልል እስከ ቀበሌ በተዘረጋ ምክርቤት የሚወስኑበት ቢሆንም ተቃዋሚዎች አለቅጥ ይውጣ ይቀየር ሱሉ ከርመዋል።አማራጭ ሲባሉ የግለሰብ መብት ከተከበረ የብሄር ብሄረሰቦች መብት ጨምሮ ሌሎች የቡድን መብቶችም የሚከበሩ በመሆኑ አላሰፈላጊ ነው በማለትም ይበልጥ አቋማቸው ስሜት አልባ አደረጉት።

2. የመሬት ጥያቄ

በመሬት ጥያቄ ላይ ህገ መንግስቱ የሰጠው መልስ እላይ ከተገለፀው አንቀፅ ጋር ከፍ ያለ ትስስር አለው።ከጋራ ማንነት ማስከበር ጋር እጅጉን የተቆራኘ ነው። ይህ የመሬት ጥያቄ በመንግስት ሆኖ የህዝቦች ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ መንገድ ተግባራዊ መሆኑ አውቀው ያደሩ ህዝቦች መሬትህ የግልህ አድርግና ሽጠህ ለውጠህ የትም ለመሄድ ይፈቀድልሃል ሲሉም ተቃዋሚዎች ሊቀሰቅሱት ሞክረዋል። እናም ኢህአዴግ ምርጫውን ሊያሸነፍ የቻለው ሕዝቡ

3. የ1920ዎቹ ጥያቄ አሁን እንመልሳለን ማለታቸው

   ተቃዋሚዎች እንደ ጉድ የተሻሙበት የመከራከሪያ አጀንዳ ቢኖር ወደብ እናስመልሳለን የሚለው ነው። እንዴት ሲባሉ መልስ የላቸውም ነበር። ምንም አይነት ህጋዊና ሰለማዊ ፍንጭ መስጠትም አልቻሉም። ሊሰጡም አይችሉም። የህገ መንግስቱ እንቀፅ 86 መርህ በአጠቃላይ የሀገር ሉአላዊነት በእጅጉ የሚፈታተን ጉዳይ እስካልመጣ ድረስ በሰላም አብሮ የመኖር መርህንና አለም አቀፍ ስምምነቶች ማክበርን ይጠይቃል።

እነዚህንና ሌሎች ጉዳዮችን ያገናዘበ አንድ ጓደኛየ የተቃዋሚዎች ክርክር ከኢህአዴግ ጋር በፖሊሲ አማራጮች የተደረገ ሳይሆን ህገ መንግስቱ ይሻሻል አይሻሻል በሚል ህዝቡ ሪፈረንደም ያካሂድ የሚል ያህል ነው ሲል የቆየው። እናም መጨረሻ የሆነው ይሀው ነው ባይ ነኝ። ተቃዋሚዎች እላይ በተገለፁትና ሌሎች የህገ መንግስቱ ምሰሶዎች ላይ ያላቸውን የይሻሻልልን የተማፅኖ ክርክር እውነትም ህገ መንግስታዊ ማሻሻያ ሪፈረንደም የመጠየቅ እንጂ የፖሊሲ ክርክር አላስመሰለውም ምርጫ 2002።

ህዝቡ ስለ ህገ መንግስቱ ቁልፍ ምሶሶዎች ለተጠየቀው ሪፈረንደም ሌላ አጀንዳ ከሌላችህ በማለት ለምክርቤት የሚያበቃ ድምፅ ነፈጋቸው። ይህ ትልቅ ትምህርት ነው። የተቃዋሚ ወገን የሆኑ ፀሃፊዎችም እያንዳንዱ ፓርቲ እየመረመሩ ከህገ መንግሰቱ ጋር የነበረው ተቃርኖ መርምረው ማሳየትና እንዳይደገም መምከር ይገባቸዋል። እኔም እንደ ዜጋ ለብዝሃ ሃሳብ ፍጭት መጎልበት የሚበጀው የጋራ መግባባት ተደርሶበት እየተጠናከረ ካለው ህገ መንግስታዊ መርሆዎች ጋር መጋጨት ሳይሆን ይነስም ይብዛም ተጨባጭ የመከራከሪያ ሃሳቦች ከአሁኑ ማሰብ ይበጃል እላለሁ።